# ገንዘብ ሚኒስቴር

## የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን
## የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2011

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

ገንዘብ ሚኒስቴር
መጋቢት 2011 ዓ.ም

# የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2011

## 1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጁ አንቀጽ 136 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፌደራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 አንቀጽ 20 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

## 2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. <u>ትርጓሜ</u>

በአዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም

1. "ታክስ ወኪል" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 96 መሠረት ፈቃድ የተሠጠው የታክስ ወኪል ነው፡፡
2. "የታክስ ወኪልነት አገልግሎት" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ታክስ ከፋዮች ከባለሥልጣኑ ጋር ለሚኖራቸው ጉዳዮች ታክስ ከፋዮችን በመወከል ከባለሥልጣኑ ጋር ማንኛውንም አይነት የሥራ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡
3. "የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ" ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

4. "የታክስ ወኪልነት ንግድ ስራ ፈቃድ" ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ መሰረት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል የሚሰጥ የንግድ ስራ ፈቃድ ነው፡፡

5. "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ታክስ ወኪሉ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ጽኑ ህመም ሲኖር እና ይህም በታክስ ወኪሉ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ሲኖረው ነው፡፡

6. "አዋጅ" ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡

7. "ደንብ" ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ ቁጥር 407/2008 ነው፡፡

8. "ሰው" ማለት ግለሰብ፣ የሽርክና ማህበር አባል ወይም ተቀጣሪ ወይም የኩባንያ ተቀጣሪ ነው፡፡

9. "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

10. "ባለስልጣን" ማለት የገቢዎችና ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን፤</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 96 መሰረት የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማግኘት ከሚፈልግ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ግለሰብ፣ ኩባንያ እና የሽርክና ማህበር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>የታክስ ወኪልነት የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስለመወሰን</u>

4. <u>የታክስ ወኪልነት የፈቃድ ደረጃዎች</u>

1. የደረጃ "አንድ" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማናቸውም ታክስ ከፋይ አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት ቁ.2 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

2. የደረጃ "ሁለት" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች በስተቀር ለሌሎች ለማናቸውም ታክስ ከፋዮች አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው።

## 5. የደረጃ "አንድ" ታክስ ወኪል ፈቃድ ለመስጠት አነስተኛ ተፈላጊ ችሎታ፤

1. በታክስ አስተዳደር፣ በአካውንቲግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት፣ በህግ ወይም በሌላ ተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ ወይም አቻ የትምህርት ዝግጅት ያለው፣

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፉት አምስት ዓመታት ፈቃድ በተሰጠው ታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት ወይም እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪል ስልጠና እንዲሰጥ እውቅና የሰጠው ተቋም የሚሰጠውን የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማውጣት የሚሰጠውን የአቅም ማጎልበቻ ኮርስ በብቃት መከታተልና መግቢያ ፈተናውን ከ 50 በመቶ (50%) እና ከዛ በላይ ውጤት ያመጣና የምስክር ወረቀት ያለው

4. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው የሽርክና ማህበር ሲሆን እያንዳንዱ የማህበሩ አባላት መልካም ጠባይና ስነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ፡

5. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው ኩባንያ ሲሆን እያንዳንዱ የኩባንያው ዳይሬክተር፤ ሥራ አስኪያጅና ሌላ ስራ አስፈፃሚ መልካም ጠባይና ስነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ

6. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ማለት በታክስ ሠራተኛነት ባለፉት አምስት ዓመታት በአገር ውስጥ ታክስ ጉዳዮች ላይ የሠራ ማለት ነው።

## 6. የደረጃ "ሁለት" የታክስ ወኪል ፈቃድ ለመስጠት አነስተኛ ተፈላጊ ችሎታ

1. በታክስ አስተዳደር፣ በአካውንቲግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት፣ በህግ ወይም በሌላ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ በዲግሪ የተመረቀ ወይም አቻ የትምህርት ዝግጅት ያለው ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance
ARCHIVES 2

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፉት አምስት ዓመታት ፈቃድ በተሰጠው በታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት ወይም እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪል ስልጠና እንዲሰጥ እውቅና የሰጠው ተቋም የሚሰጠውን የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማውጣት የሚሰጠውን የአቅም ማጎልበቻ ኮርስ በብቃት መከታተልና መግቢያ ፈተናውን ከ 50 በመቶ (50%) እና ከዛ በላይ ውጤት ያመጣና የምሥ ክር ወረቀት ያለው፣

4. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው የሽርክና ማህበር ሲሆን እያንዳንዱ የማህበሩ አባላት መልካም ጠባይና ስነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ፡

5. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው ኩባንያ ሲሆን እያንዳንዱ የኩባንያው ዳይሬክተር፤ ሥራ አስኪያጅና ሌላ ስራ አስፈፃሚ መልካም ጠባይና ስነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ማለት በታክስ ሠራተኛነት ባለፉት አምስት ዓመታት በአገር ውስጥ ታክስ ጉዳዮች ላይ የሰራ ማለት ነው፡፡

## 7. <u>ለታክስ ወኪልነት ሙያ ብቁና ተስማሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች መስፈርቶች</u>

ማንኛውም ግለሰብ፣ የኩባንያ ተቀጣሪ፣ የሽርክና ማህበር አባል ወይም ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት፤

1. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ እና ዕድሜው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ ሰው፣

2. ከታክስ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ወንጀል በመፈፀሙ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠ፤

3. የሙያ ኃላፊነት መድህንን ዋስትና ለማስያዝ አቅም ያለው፣

4. በጽሁፍ ቃለ-መሐላ መፈጸም የሚችል

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

## 8. <u>በታክስ ወኪልነት ሙያ በሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ ስለመስራት</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4፣ 5፣ 6 እና 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ወኪልነትን በሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ መሥራት የሚቻለው ከሁለት ያላነሰ የታክስ ወኪሎች ሲኖራቸው ብቻ ነው፡፡

2. የሽርክና ማህበሩ ወይም ኩባንያው ቢያንስ አንድ ቡድን ያለውና የተሻለ አገልግሎት ለመሥጠት የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ያለው መሆን አለበት፡፡

3. በሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ስራ አስኪያጅ እና ሌላ ስራ አስፈፃሚ ባለስልጣን ተቀጣሪዉ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ፣ መልካም ጠባይና ስነ-ምግባር ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

4. ባለሥልጣኑ የሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ የሚሰጡትን የአገልግሎት ዓይነት እና ብዛት፣ የተገልጋዩን ብዛት በማየት በድርጅቱ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የታክስ ወኪሎች ቁጥር ሊወስን ይችላል፡፡

## 9. <u>ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ሰው የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲሰጠው ባለስልጣኑ ለዚሁ አላማ ባዘጋጀው የጸደቀ ቅጽ በመጠቀም ማመልከት አለበት፡፡

2. ባለስልጣኑ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ላመለከተ ሰው አነስተኛ ተፈላጊ ችሎታና ሌሎች መስፈርቶች ማሟሏቱን በማረጋገጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1ና 2 የተደነገጉትን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

4. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሙያ ፈቃድ በመሆኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚሁ የሥራ መስክ የንግድ ስራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደሆነ በዚህ ፈቃድ ስራውን የሚሰራው በታክስ ወኪልነት ብቻ ነዉ፡፡

5. በባለስልጣኑ የተሰጠ የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆነው በፌደራል፣በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬደዋ አስተዳደር ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

Ministry of ARCHIVES 2 Finance
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

6. ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ በየጊዜው ይፋ ያደርጋል።

## 10. <u>የታክስ ወኪሎችን ፈቃድ ስለማደስ</u>

1. ማንኛውም የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲታደስለት የሚፈልግ የታክስ ወኪል የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲታደስለት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት 21 ቀናት ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ በዘገየ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ለዚሁ ዓላማ ባዘጋጀው የጸደቀ ቅጽ በመጠቀም ማመልከቻ ማቅረብ አለበት

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ማሳደስ ያልቻለ ታክስ ወኪል የታክሰ ወኪልነት ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ድረስ ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪሉን ማመልከቻ ተቀብሎ ፍቃዱን ሊያድስለት ይችላል።

3. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ዓመታት የሚፀና ሲሆን በየሶስት አመቱ መታደስ ይኖርበታል

4. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ወኪሉ ወይም ተቀጣሪው በባለስልጣኑ እውቅና በተሰጠው ተቋም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዕስ አንቀጽ 3 መሰረት ሥልጠና መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው።

5. ለዚህ አንቀጽ 9 እና 10 አፈጻጸም ባለሥልጣኑ በራሱ የሚሰጠውን ወይም በባለሥልጣኑ የተወከሉ ድርጅቶች የሚሰጡትን የሥልጠና አይነትና ይዘት ይወስናል።

## 11. <u>የታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

1. የታክስ ወኪልነት ስራው በጊዜያዊነት እንዲቋረጥ የፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ስራውን ከማቋረጡ በፊት በ7/በሰባት ቀናት/ ውስጥ የሚያቋርጥ መሆኑን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም የታክስ ወኪል ፈቃድ በጊዜያዊነት ሊቋረጥ የሚችለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቡ.ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

3. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በቋሚነት በታክስ ወኪልነት መስራት ካልፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃዱ እንዲሰረዝለት ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል፡፡

4. ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ ይችላል፡፡

    ሀ) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ተዘጋጅቶ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ በማንኛውም መሰረታዊ ጉዳይ ሀሰት ሆኖ ሲገኝ፤

    ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማግኘት የሚጠየቁና የሚያስፈልጉ የብቃት መስፈርቶችን ይዞ መቀጠል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ወይም ባለስልጣኑ የታክስ ወኪሉ ሙያዊ የስነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን፣

    ሐ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ስራዉን መስራት ሲያቆም፣ እንዲሁም የታክስ ወኪሉ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማህበር ሲሆን የኩባንያው ወይም የሽርክና ማህበሩ ህልውና ሲያከትም፣

    መ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲሰረዝለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

    ሠ) የታክስ ወኪሉ የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ እና የታክስ ወኪሉ ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከቻ ሳያቀርብ ሲቀርና በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀጽ 5/ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ካልታደሰ፣

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ባለስልጣኑ የታክስ ወኪሉ ፈቃድ የተሰረዘ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ በመስጠት ለህብረተሰቡ በሚያመች መንገድ ስለመሰረዙ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

6. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ የሚፀናው፡-

    ሀ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ስራውን መስራት ካቆመበት ቀን ወይም

    ለ) ፈቃዱ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ ከተሰጠ ከ60 /ከስልሳ/ ቀናት በኃላ፣ ከሁለቱ ቀድሞ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

7. ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሙያዊ የስነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን ይህንን የስነ-ምግባር ጥሰት፡-

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

ሀ) ለኢትዮጵያ የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት፤ ለኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም እንደ አግባባነቱ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሂሳብ ባለሙያነት፣ የኦዲተርነት ወይም የሕግ ባለሙያነት ፈቃድ ለሰጠው ሌላ አካል እና

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊነት ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ያደርጋል።

## ምዕራፍ ሦስት

## <u>የታክስ ወኪሎች ስልጠናን ስለመወሰን</u>

### 12. <u>የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለመስጠት ለሚያስችል ስልጠና ጥሪ ስለሚቀርብበት ሂደት</u>

1. ባለሥልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣው ፕሮግራም መሰረት አነስተኛውን የተፈላጊ ችሎታ መስፈርቶቹን አሟልቶ የሚያቀርብ ማንኛውንም የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ተመዝጋቢ ለሥልጠና ይመለምላል።

2. በታክስ ወኪልነት የሙያ ስልጠና ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ጥሪ ለማድረግ በገቢዎች ሚኒስቴር ቅ/ጽ/ቤት ወይም ውክልና ከተሰጠው ተቋም ከሚለጠፍ ማስታወቂያ በተጨማሪ ባለሥልጣኑ ጥሪው አገራዊ ስርጭት ባለው መገናኛ ብዙሀን /ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን/ እንዲነገር ያደርጋል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረቡት አመልካቾች ብዛት ከማሰልጠኛ ተቋሙ አቅም በላይ ከሆነ ባለሥልጣኑ በተመዘገቡበት ቅደም ተከተል መሰረት ሥልጠናውን እንዲያገኙ ያደርጋል፣

4. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት ቢኖሩም ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪል ለማሰልጠን ፈቃድ በተሰጠው ተቋም ምልመላውና ሥልጠናው እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል።

### 13. <u>የታክስ ወኪልነት ስለሚያካትታቸው የሥልጠና ርዕሶች</u>

1. ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስልጠና የሚያካትታቸውን የሥልጠና ዓይነቶችንና ርዕሶችን ይወስናል።

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ባለስልጣኑ በሚወስናቸው የሥልጠና ርዕሶች ቢያንስ ለ240 ሰዓት ስልጠና መውሰድ ይጠበቅበታል።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማደስ የሚቀርብ ሰው ባለስልጣኑ በሚወስነው የስልጠና ርዕስ ቢያንስ 120 ሰዓት ስልጠና መውሰድ ይኖርበታል፡፡

## 14. <u>የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት ስለሚሰጥ ፈተና</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት የታክስ ወኪልነት ስልጠና ወስዶ ያጠናቀቀ ማንኛውም ሰው የጽሑፍ ፈተና ይሰጠዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጽሑፍ ፈተና የወሰደ ሰው የታክስ ወኪልነት የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከ50 በመቶ (50%) በላይ ውጤት ማምጣት ይኖርበታል
3. ባለሥልጣኑ ለታክስ ወኪልነት የሚሰጠውን ፈተና ይዘት ይወስናል፡
4. እያንዳንዱ ሰልጣኝ ለሥልጠናው የሚከፍለው የገንዘብ መጠን በየሥልጠናው ወቅት በባለሥልጣኑ የሚወሰን ይሆናል፣

## ምዕራፍ አራት

## <u>የታክስ ወኪል የሥነ ምግባር መርሆች እና አስተዳደራዊ ጥፋት</u>

## 15. <u>የታክስ ወኪል የሚመራበት የሥነ ምግባር መርህ</u>

ማንኛውም የታክስ ወኪል፣

1. በታማኝነት ማገልገል
2. ራስን ከጥቅም ግጭት ማግለል
3. ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
4. ህግን ማክበር እና ማስከበር
5. ሚስጥር መጠበቅ
6. ለሙያው ብቁ ሆኖ መገኘት፣ አለበት፡፡

## 16. <u>ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል ኃላፊነት</u>

ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል፣

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

1. የሁሉንም ደንበኞቹን ስም፣ ከደንበኞቹ ጋር የፈጸመውን የስራ ውል፣ የደንበኞቹን ቋሚ፣ የፖስታ ወይም ሌሎች አስፈላጊ አድራሻዎች፣ደንበኞቹ የተሰማሩበትን የንግድ ወይም የስራ አይነት የያዘ መረጃ እና፣

2. ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጨማሪ የመጨረሻው የታክስ ተመላሽ ወይም የታክስ ማስጠንቀቂያ ለተገልጋዩ የተሰጠበትን ቀን፣የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን የታክስ ደረሰኝ ቁጥር እና ሌሎች መረጃዎች የያዘ ቋሚ መዝገብ የመያዝ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች መያዝ እና በባለስልጣኑ ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት።

## 17. ስለሥራው የሚያስፈልገውን የመድህን ዋስትና ስለመወሰን፤

በታክስ ወኪልነት ለመሰማራት የሚያስችለውን ፈተና በብቃት የተወጣ የታክስ ወኪል በሚከተለው አኳኋን የመድህን ዋስትና ማቅረብ አለበት።

1. ለደረጃ አንድ የታክስ ወኪል ፈቃድብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለደረጃ ሁለት የታክስ ወኪል ፈቃድ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/፣

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰውን የመድን ዋስትና የገንዘብ መጠን እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል።

## 18. የአሠራር ሥርዓት ስለመዘርጋት

ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት ወይም አደረጃጀት ሊዘረጋ ይችላል።

## 19. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም አሠራር በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

## 20. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።፡

አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of
ARCHIVES
2